# የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና ተያያዥ ችግሮቹ

05-11-15

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከኮንጎ ዴሞክራክቲክ ሪፐብሊክ በመቀጠል ሁለተኛዋ ግዙፍ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም ያላት ሀገር ነች፡፡ ይህን ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም ወደ እውነታነት ለመቀየርና አገልግሎት ላይ ለማዋል በሚደረግ ጥረት በተግባራዊ እንቅስቃሴ ጭምር በማሳየትም ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ስሟ እየተነሳ መጥቷል፡፡

በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት ጅማሮ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ታሪክ አለው፡፡ ዘርፉ ስድስት አስርት ዓመታት ያስቆጠረና ዘመናዊ ሊባል የሚችል የአገልግሎት ተቋም ደረጃ ላይ መድረስ የነበረበት መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች የሚያመላክቱ ቢሆንም ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በፊት ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ማግኘት አዳጋች የነበረበት፣ የአብዛኞቹ የሀገራችን ከተሞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነት ውስን የነበረበትና ህብረተሰቡም ከዘርፉ በሚገኘው ጥቅም ህይወቱን እንዳይለውጥ የተገደደበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ዘርፉ ይነስም ይብዛም ሀገሪቱ አሁን ላለችበት የእድገት ደረጃ የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከቱ የማይካድ ቢሆንም ከሀገራችን የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት አጀማመር የጊዜ ርቀት አንፃር ወቅቱ የሚጠይቀውን የሰው ሃይልና የቴክኖሎጂ አቅም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሳይገነባ ቆይቷል፡፡ ሀገሪቱ ባለፈችባቸው በተለያዩ መንግስታት በተለያዩ መዋቅሮች ማለፉና ከዘርፉ የሚገኘውን ትርፍ ብቻ ታሳቢ ያደረገ አሰራር እንዲሁም የአገልግሎቱን ጥራት ለማሻሻል የተደረጉ ጥረቶች አለመኖራቸው አሁን ላለንበት የአገልግሎቱ ችግሮች መባባስ አድርሶናል፡፡

የሀገሪቱ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትና የህዝብ ቁጥር እንዲሁም የኢኮኖሚው እድገት የፈጠረው የዜጎች የዘመናዊ ኑሮ መሻት የኤሌክትሪክ ፍላጎትን በከፍተኛ ደረጃ እያናረው ይገኛል፡፡ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው ግብርናም ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ማደግ የራሱን ድርሻ በማበርከት ቦታውን ለማኑፋክቸሪንግና ለኢንዱስትሪ መልቀቅ መጀመሩ የሀይል ፍላጎትን እንዲያሻቅብ ምክንያት እየሆነ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች በተለይም እንደ ኮንስትራክሽን ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችም የሚጠበቅባቸውን የኢነርጂ አቅርቦት ለማሟላት ከመቼውም ጊዜ በላይ የሀይል ዘርፉን በሰው ሃይልና በቴክኖሎጂ አቅም መገንባት እንዲሁም የሀይል ማመንጫ ግድቦችን ማስፋፋትና አቅማቸውን ማሳደግ ይገባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ለኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነውን የኢነርጂ ልማት ባለፉት ዓመታት የተለየ ትኩረት በመስጠት በማልማት ላይ የሚገኝ ሲሆን ባለፉት ሀያ ዓመታት ብቻ ወደ ስምንት የሚጠጉ የሀይል ማመንጫ ግድቦችን አስገንብቷል። የግል ባላሀብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ እያበረታታ ይገኛል፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ ታላላቅ የሚባሉ የሀይል ማመንጫ ግድቦችን በመገንባት አስተማማኝና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆኑት በመገንባት ላይ ያሉት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኃይል ማመንጫ ግድብ፣ የጊቤ ሶስት የኃይል ማመንጫ ግድብ፣ የገናሌ ዳዋ ሶስትና የአዳማ ሁለት የንፋስ ኃይል ማመንጫ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ዘርፉ ያሉበትን ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመፍታት የተለያዩ እቅዶችን ነድፎ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ከሀገሪቱ ፈጣን ዕድገት ጋር ተያይዞ እያደገ የመጣውን የሀይል ፍላጎት ለማርካትና ተደራሽነቱንም ለማሳደግ እንዲሁም ዘመናዊና ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል የሀይል ዘርፉ እንደ አዲስ እንዲደራጅ ብሎም እንዲዘምን የቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን በመባል የሚታወቀውን ለሁለት በመክፈል የየራሳቸው ህልውና ባላቸው ሁለት የስራ ዘርፎች ወይም ካምፓኒዎች እንዲዋቀር በማድረግ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል እና የኤሌክትሪክ አገልግሎት በሚል ስያሜ በደንብ እንዲቋቋሙ አድርጓል፡፡

## <u>የኃይል መቆራረጥና ችግሮቹ</u>

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሀገሪቱ ዋና ዋና በሚባሉ ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ የኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት በየቀኑ በተደጋጋሚ የመጥፋት ለቀናትም የመቆየት ሁኔታ እየተስተዋለ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሀገሪቱ የምታመርተው የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ከፈጣን የኢኮኖሚ እድገቱ ጋር በቂ ነው ባይባልም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ችግሩ የኤሌክትሪክ ምርት እጥረት ወይም የማመንጫ ችግር አለመሆኑን በርካታ ማሳያዎች አሉ፡፡

የዚህ ቁልፍ ችግር መነሻ ምክንያቶችን እንዲሁም ችግሮቹን በዘላቂነት በመፍታቱ ረገድ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ምን እንደሚመስሉ እንቃኛለን፡፡

የኤሌክትሪክ ሃይል ከማመንጫ ግድቦች በተርባይን አማካኝነት የሚመነጨውን ኤሌክትሪክ ወደ ተጠቃሚው ሊያደርሱ በሚችሉና ከፍተኛ ህዝብ በሚገኝባቸው በሚገነቡ ንዑስ የማከፋፊያ ጣቢያዎች (sub-stations) በመግባት ከዚያም ወደ ማሰራጫ መስመሮች በመሸጋገር ለተጠቃሚው የሚደርስ ነው፡፡ ኤሌክትሪኩን ከማምረት አንስቶ ለማስተላለፍና ለማሰራጨት ከሀይል ማመንጫ ግድቦች ወይም ጣቢያዎች እስከ የተዘረጉ ልዩ ልዩ መጠን ያላቸው የማስተላለፍያና የማሰራጫ መስመሮች፣ ትራንስፎርመሮች በአጠቃላይ ተቋማቱን አቀናጅቶ የኤሌክትሪኩን ምርትና ስርጭት ለ24 ሰዓታት ሳይቋረጥ እንዲዘልቅ የሚሠሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ባለሞያዎች ያሉበት ሂደት ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ስርዓት እንደ ማስተላለፍያና ማከፋፈያ መስመሮቹ ሁሉ የተጠላለፈና የተወሳሰበ ግዙፍ የሚባል የሰው ሀይልና በምህንድስና ዘርፍ የተማረ የሰው ሀይል አቅም የሚጠይቅ ቴክኖሎጂ ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው፡፡

በየትኛውም የአለማችን ክፍል ለኤሌክትሪክ መቆራረጥ ምክንያት ተብለው የሚወሰዱ ጉዳዮች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ እንደየሀገራቱ አቅምና የደረሱበት የእድገት ደረጃ የተለያዩ ቢሆንም እንደዚሁ በርካታ ናቸው፡፡ ይሁንና ለጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰዓታት እንዲሁም ለቀናት በውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች የኤሌክትሪክ ሀይል ሰርዓት መዛባት የሚከሰት ተብለው በሁለት ጎራ ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ በሀገራችን ሁለቱም ችግሮች በስፋት የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን የተወሰኑትን ለመመልከት ያህል፡-

አንደኛው ችግር ከቴክኒክ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቴክኒካዊ ችግር ምክንያቱ ከፕላንና ከምህንድስና ጋር ይያያዛል፡፡ አሁን ያለው የአገልግሎት አሰጣጥና የፓወር ሲስተም ቴክኖሎጂ የረቀቀበት ደረጃና ያለው አቅም እየተጣጠመ ያለመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ዋናው ቁልፍ ችግር የሚባለው ከኤሌክትሪክ ማምረት፣ ማስተላለፍና ከማሰራጫ አቅም ጋር የተያያዙ ችግሮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ የስርጭት መስመሮች አቅም ከማስተላለፍያ መስመሮች አቅም ያነሰ ነው፡፡ ለምሳሌ ሊያመርት የተዘጋጀው የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ 100 ሜጋዋት ሊሆን ቢችል ያንን ሊያሰተናግድ

የሚችል ወደ ሰብ ስቴሽን ሊያሰገባ የሚችል የከፍተኛ ቮልት አቅም ያላቸው የማስተላለፍያና ከዚያም ወደ ተጠቃሚው ሊያደርስ የሚችል የዝቅተኛ ቮልት የማከፋፈያ መስመሮች መኖር የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ወይም እንዳይቆራረጥ ከሚያደርጉት ጉዳዮች ዋናው እንደሆነ በባለሞያዎቹ ይገለፃል፡፡

የኤሌክትሪክ ማስተላለፍያ ትራንስፎርመሮችም አቅም ሌላኛው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በየትኛውም ዓለም ቢሆን የኃይል ማሰራጫ መስመሮችም ሆኑ ትራንስፎርመሮች እንዲሁም ፖሎች የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ አላቸው፡፡

የማስተላለፊያ ኔትወርክ ስርዓቱ የስርጭት ኔትወርክ ስርዓቱን እንዳያውክ፣ ጤናማ የሆነ ያልተቆራረጠ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከማመንጫ ጣቢያ አንስቶ እስከ ማስተለለፍያ ብሎም እስከ ማከፋፈያና ቤት ድረስ እንዲደርስ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በኤሌክትሪክ አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ሳይነሱ የሚለው የማከፋፈያ መስመሮች አቅም ከማስተላለፍያ መስመሮች አቅም የበለጠ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ ይሁንና በሀገራችን ከሀይል ማመንጫ ጣቢያዎች በማስተላለፍያ መስመሮች አማካኝነት የሚጓጓዘውን የኤሌክትሪክ ሃይል ሽክም በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ የስርጭት ኔትወርክ ስርዓቱ ጤናማ እንዲሆን የሚያስችል የስርጭት መስመሮች አቅም አናሳ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት አንድም የማሰተላለፍያና የማሰራጫ መስመሮች የአገልግሎት ጊዜያቸው አብቅቶ ስራቸውን በአግባቡ መከወን አለመቻላቸው ሲሆን ሌላው በተቋሙ በኩል ወቅቱን የጠበቀ የመሳሪያዎች ጥገናና የመተካት ስራ አለማከናወን እንዲሁም ግንባታዎቹን ለማከናወን የሚጠይቁት የፋይናንስ አቅም ማነስ ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ፡፡

ሁለተኛው ችግር ከመጀመርያው ችግር ጋር አብሮ የሚሄድና ካረጁ ወይም ማርጀት ከጀመሩ የማስተላለፍያ መስመሮች ጋር የታያያዘ ሲሆን በቀጥታ የማከፋፈያ ጣቢያዎች (sub-stations) ላይ ባሉና ባልተቀረፉ ችግሮች ነው፡፡ ባለፈው ዓመት ብቻ በ43 የማከፋፈያ ጣቢያዎች ላይ በተደረገ ጥናት ወይም ግምገማ ወደ ሃምሳ (50) የሚደርሱ ትራንሰፈርመሮች የሀይል መጨናነቅ እንደገጠማቸው ተስተውሏል፡፡ በዚህም ትራንሰፎርመሮቹ ሀይል መሸከም ከሚችሉት አቅም ማለት ከመቶ ፐርሰንት በላይ ጫና በመፈጠሩ ወደ ስርጭት ኔትወርክ ስርዓቱ የሚገባውን የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲያዛባው ምክንያት ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ ችግሩ ሲገነባ የቆየው ሲስተም የፈጠረው ችግር ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ሦስተኛው የሀይል ፍላጎት አሁንም በመጨመር ላይ ነው፡፡ የማስተላለፍያ መስመሮች ግንባታ በሚፈለገው ፍጥነት ያለመሄዱ ከማመንጫ ጣቢያዎች የሚመረተውን ሃይል በሚፈለገው

መንገድ በማሰራጨቱ ረገድ አሉታዊ ተፅዕኖ አበርክቷል፡፡ ግንባታዎች በወቅቱ ተገንብተው ያለመጠናቀቅና በውሉ መሠረት አገልግሎት ከሚሰጠው ጋር ርክክብ ባለመፈፀሙ ኤሌክትሪክ ለማግኘት ተመዝግበው የሚጠባበቁ ደንበኞችን፣እንዲሁም በኤሌክትሪክ አገልገሎት ስርዓቱ ውስጥ ቀድሞ የነበሩትንም የሚጎዳ አሰራር በመሆኑ በአፋጣኝ መቀረፍ ያለበት ችግር ነው፡፡

ከሀይል ፍላጎት መጨመር ጋር በተያያዘ ያለው ሌላኛው ሁኔታ ሲቃኝ በአዲስ አበባ ብቻ የኢንዱስትሪዎችን ሳይጨምር የ 2007 ዓ.ም የገና በዓል በፊት ከነበረው በተለየ መልኩ የሀይል ፍላጎቱ ወደ 150 ሜጋ ዋት አድጓል፡፡ ከዓመት በፊት የነበረው የከተማዋ የኤሌክትሪክ ሃይል ፍላጎት ከ 15-33 ሜጋ ዋት የነበረ ሲሆን ዘንድሮ በተደረገ ጥናት የኤሌክትሪክ ሃይል ፍላጎቱ በአማካኝ ከ30-80 ሜጋ ዋት ደርሷል፡፡

ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ሲቃኝ የስርጭት አቅም ካለው የኃይል ፍላጎት ሁለት እጥፍ በልጦ መገኘት አለበት የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት የሚመነጭ የኃይል አቅም አገልግሎት ላይ ሊውልና የስርጭት አቅም ሊሸከመው ከሚችለው የስርጭት ኔትወርክ አቅም ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለአብነት ያህል የኢትዮጵያን የስርጭት ኔትወርክ አቅምን ካየን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ለሁለት ተከፍሎ የአገልገሎት ዘርፉ ስራውን በጀመረበት ወቅት የነበረው የኤሌክትሪክ ስርጭት ኔትወርክ አቅም ከ13-18 ሜጋ ዋት ነበር፡፡ አሁን ያለው ግን ከ60-180 ሜጋዋት የሚደርስ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ 80 በመቶ በየዓመቱ ወደ ስርጭት ኔትወርክ ስርዓቱ ባልተገባ መንገድ ማለትም የኤሌክትሪክ ሃይል ሊያስተላልፍ የሚችል የትራንስሚሽንና የስርጭት አቅም በሌለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የሚፈለገውን የኤሌክትሪክ ኃይል ሊሸከም የሚችል የማስተላለፊያና የማከፋፈያ ኔትወርክ አቅም በሌለበት የተወለደ ፍላጎት ተብሎ የሚገለፅ ሲሆን ለመኖርያነት በተከለሉ አካባቢዎች የሚከናወኑ የትላልቅ ህንፃዎች ግንባታ ለፍላጎቱ ማደግና ለኤሌክትሪክ

አገልግሎት መቆራረጡ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ የስርጭት አቅማቸው ከፍተኛ የሆኑ መስመሮችን በመጠቀም ከዝቅተኛ አቅም ያላቸው መስመሮች ጋር የማቀያየር ስራ በመስራት አገልግሎት መስጠት የሚያስችልም የኤሌክትሪክ ሃይል የኔትወርክ ስርዓት (system redundancy) ባለመኖሩ ችግሩን በመፍታቱ በኩል አዳጋች ሆኗል፡፡

አራተኛው ለሀይል መቋረጥ ምክንያት የሚሆነው ሰብስቴሽን ላይ ያሉ መስመሮች በስርጭት ኔትወርክ ስርዓቱ ላይ በሚፈጥሩት የሀይል ጫና ሲሆን ይህም የትራንስፎርመሮችን መቃጠል ሁሉ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ትራንስፎርመሮች በሚቃጠሉበት ወቅት ለመተካት በሚደረገው ሂደት አገልግሎት ሊቋረጥ ይችላል፡፡ እንደዚሁ በሀይል መስመሮች ላይ በፕሮግራም በሚከናወን የጥገና ሂደት ውስጥም አገልግሎት ላይኖር ይችላል፡፡ ስለሆነም የሀይል አገልግሎት የሚቋረጥባቸው በርካታ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የኤሌክትሪክ ሀይል ቁሳቁሶችም በሚፈለገው ደረጃ ባለመቅረቡ የሀይል መስመሮቻችንን እያስታመምን የምንቀጥልበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ዘላቂ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ችግሩን በጊዚያዊነት ለመፍታት ይሞከራል፤ ውሎ አድሮ ግን ችግሩ እየተደጋገመ አገልግሎት ፈላጊውን ህብረተሰብ የሚያማርር ይሆናል፡፡

አምስተኛው በሰው ኃይል በኩል ያለው ነው፡፡ ያለው የሰው ሃይል በአስተሳሰብ ረገድ ብዙ የሚቀረውና የዘርፉን ቴክኖሎጂን ሊያንቀሳቅስ የሚችል ሳይሆን ቆይቷል፡፡ የሰው ሃይል አስተሳሰብ ለደንበኛ ከሚሰጠው አገልግሎት፣ አገልግሎቱ ካለው ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና አስተዋጽኦ በመነሳት በሙሉ ፍላጎት ለመስራት ያለው አቅም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህንን ክፍተት በተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ዘዴዎች መሙላት፣ ደንበኛ ተኮርና ጥራት ያለው የሰው ሃይል መገንባትና አገልግሎቱን ፈጣን፣ተደራሽና ጥራት ያለው ማድረግ ይገባል፡፡

ሌላኛው ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሠራተኛው በኤሌክትሪክ ጥገና ወቅት የሚፈጠሩ አደጋዎችን መከላከል በሚያስችሉ የመከላከያ ቁሳቁሶች ያለመደራጀት እንዲሁም እንደ ትራንስፎርመር ፊደር (transformer feeder) ያሉ የመለዋወጫ መሳሪያዎች አቅርቦት በሚፈለገው ጊዜና ቦታ ያለመኖር ችግር የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ጥራትና ተደራሽነት ፈተና ላይ የጣሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ከላይ የተገለፁት ችግሮች በአጠቃላይ ተደማምረው የሃይል ዘርፉ ውስብስብ ችግሮችን የሚያሳዩ ሲሆን የሀገሪቱን እድገት በማስቀጠል ወይም በማደናቀፍ በኩልም የራሳቸው ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የተሟላ የሀይል አቅርቦት ለኢኮኖሚው ተጨማሪ እሴት በመፍጠር ሀገሪቱ የተያያዘችውን ድህነትን የመቀነስ ስትራቴጂ በማገዝ የሚኖረው ሚና ቀላል የሚባል እንዳልሆነ የሀይል ዘርፍ የምጣኔ ሀብት ባለሞያዎች ይገልፃሉ፡፡ በአንፃሩ የኤሌክትሪክ ሃይል መቋረጥና በሚፈለገው መጠን አለመኖር በኢኮኖሚው የፍጥነት ግስጋሴ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ አሌ የማይባል ሀቅና ዜጎች ማምረት የሚገባቸውንና ለኢኮኖሚው ማበርከት የሚገባቸውን አዎንታዊ ሚና የሚያኮላሽ እንደሆነ ይነገራል፡፡

በተደጋጋሚ ጊዜ በሚከሰተው የሃይል አቅርቦት ማነስ ወይም መቋረጥ/መቆራረጥ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ማምረት ከሚገባቸው በታች እንዲያመርቱ የሆነ ሲሆን በኤሌክትሪክ የሀይል መዋዠቅና መቆራረጥ የማሽኖችና የምግብ ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸው ምርቶችን ብልሽትም አስከትሏል፡፡ የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት በዜጎች የኑሮ ዘይቤና መሻሻል ላይ የሚያመጣው አዎንታዊ ለውጥ እንዳለ ቢታወቅም የችግሩ ገፈት ቀማሽ በተለይም ህይወታቸውን ከኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ጋር ያስተሳሰሩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ተቋማት ክፉኛ እንደሚጎዱ ይታመናል፡፡ በዚህ ረገድ በአዲስ አበባና በአቅራቢያው የሚገኙ ወደ አንድ መቶ ሃምሳ (150) የሚጠጉ የከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች፣ በጥቃቅንና አነስተኛ፣ በአገልግሎትና ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ተጎድተዋል፣ ለኪሳራም ተዳርገዋል፡፡

## ችግሩን ለመቅረፍ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች

የኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ መሠረታዊ ችግሮችን በመፍታት አገልግሎት አሰጣጡ የሚያረካ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማድረግ ለነገ የማይባል ተግባር ነው፡፡ ዜጎች አገልግሎቱን በተመጣጣኝ ዋጋና በጥራት የማግኘት መብቶቻቸው እንዲከበሩ እንዲሁም ተቋሙ ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት በመስጠት ትርፋማ እንዲሆን የማስቻል ተግባራትን ማከናወን የመንግስት ግዴታ

ይሆናል፡፡ ስለሆነም ችግሩን በዘላቂ መንገድ ለመፍታት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ምን እንደሚመስሉ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ለማየት ይሞከራል፡፡

አንደኛ የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥ ወይም መቆራረጥ በተደጋጋሚ የሚከሰትባቸውን ቦታዎች የመለየትና ችግሮቹ የሚቀንሱበትንና የሚፈቱበትን አሰራር የመዘርጋት ስራ ነው፡፡

የተዘረጉና የሚዘረጉ መስመሮች ሀይል ሊሸከሙ በሚችል መልኩ መገንባት ከመፍትሄዎች ሁሉ ቀዳሚውና ዋነኛው ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ሃይል በማስተላለፍያ መስመሮች አማካኝነት ወደ ንዑስ ማከፋፈያ ጣቢያዎች (sub-stations) እንዲገባ የተለያዩ የቮልቴጅ መጠን ያላቸውን የማስተላለፍያ መስመሮችን አቅም ማጠናከር ያረጁትንም በአዲስ የመተካት ስራው በአጭርና በረጅም ጊዜያት እቅድ ውስጥ ገብቶ እየተከናወነ ነው፡፡

ሁለተኛው የአዲስ አበባን የሀይል ፍላጎት አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመፍታትና የኤሌክትሪክ ሀይል መቆራረጥን ለማስወገድ ልዩ ኮሚቴና ተጠባባቂ ሃይል በማዋቀር እይተሰራ ነው፡፡ የአደረጃጀትን ችግርንም ለመፍታት በሚያስችል መልኩ በአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ስልክ የሚቀበሉ፣ መልዕክት የሚያስተላልፉና ለሚደርሱ ችግሮች የጥገና መፍትሄ የሚሰጡ ባለሞያዎች ተመድበው በተጠንቀቅ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በቆቃና በፊንጫ የሀይል ማመንጫ ግድቦች የሶስት የማመንጫ ዩኒቶች አቅማቸው ከፍ እንዲል የማሻሻያ ስራ ተከናውኖላቸዋል፡፡

በማከፋፈያ ወይም በማሰራጨት በኩል የአዲስ አበባን ችግር ለመፍታት የሚያስችል በአቃቂ ባለ 400 ኪሎ ቮልት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ እየተገነባ ሲሆን በሰበታም ያለውን ጣቢያ የማስፋፋት ስራ እየተከናወነ ነው፡፡

ሶስተኛ በእቅድ እየተሰራ ያለው በ 2007 በጀት ዓመት ለኢትዮ ቴሌኮም ታወር የኃይል አቅርቦት የሚውል የ4074 ኪ/ሜ መካከለኛ ቮልቴጅ መስመር መዘርጋትና 2716 የዲስትሪቢውሽን ትራንስፎርመር ተከላ ሥራዎች የታቀዱ ሲሆን በዕቅዱ መሰረት በመከናወን ላይ ነው፡፡ በሚቀጥሉት ዓመታት ወደ 125 ሺ ኪሎ ሜትር የከፍተኛ ቮልት ተሸካሚ የመስመር ዝርጋታ በተጨማሪነት ወደ ስርጭት ኔትወርኩ የሚገባ ይሆናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ወደ ማሰራጫ ኔትወርክ የሚገባው የዝቅተኛ ኪሎ ቮልት ተሸካሚ መስመሮች ወደ 189 ሺ ኪሎ ሜትር ደርሷል፡፡

### በቀጣይ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች

በአጠቃላይ በኤሌክትሪክ አገልገሎት ዘርፍ ያሉት ችግሮች በማከፋፈያ መሰመሮች ላይ በሚፈጠር ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ጭነት፣ የመሠረተ ልማቶቻችን ያሉበት ደረጃና አሁን ያለንበት የሀይል ማሰራጫ መሰመሮች ቅየራ የኔትወርክ ችግር፣ የመሠረተ ልማቶቹና የከተሞቻችን እድገት የተመጣጠነ ያለመሆን፣የሰው ሃይልና የቴክኖሎጂ አቅም ችግር፣ፈጣንና

ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ የአደረጃጀትና የአሰራር ችግር፣ የግብዓትና የጥገናና ኦፕሬሽን አቅም ማነስ ለኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት ጥራት መጓደል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የሀይል አቅርቦት ፍላጎትን በዋናነት የሚወስኑት የኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ የከፍተኛ ቤቶች ኮንስትራክሽን በተለይም የኮንዶሚኒየም ቤቶች የኤሌክትሪክ ሀይል ፍላጎት፣ ኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማሩ የከፍተኛ ኤሌክትትሪክ ሀይል ተጠቃሚዎችና በንግድ ላይ የተሰማሩ ውሃና ኢነርጂን ለመስኖና ለሌሎችም አገልግሎት የሚጠቀሙ ባለሀብቶች በመሆኑ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ተጨማሪ አምስት ሺህ (5000) ሜጋ ዋት ሊደርስ የሚችል ፍላጎት ሊፈጠር ይችላል የሚል ግምት አለ፡፡

አሁን የምንገኝበትን 2268 ሜጋ ዋት የሀይል ማመንጨት አቅም ወደ አስር ሺህ (10,000) ሜጋዋት ለማድረስ የሌት ተቀን ጥረት ውስጥ የምንገኝ ሲሆን የሀይል ፍላጎቱን ከመሠረተ ልማት ግንባታዎቻችን ጋር የተጣጠመ ማድረግ ግድ ይላል፡፡ በዚህ ረገድ የሃይል ማመንጫዎች ተገንብተው ከመጠናቀቃቸው በፊት የሚከናወኑ ተግባራት የሀይል መቆራረጡን በመቀነስ ረገድ ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በሁሉም ባለድርሻ አካላት በተለይ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል፣ በኮንስትራክሽን ሚኒስቴርና በከተማ ማዘጋጃ ቤቶች፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና በኢንዱስትሪ ባለቤቶች እንዲሁም እንደ ባቡርና ቴሌኮም ያሉ ምንጊዜም የኤሌክትሪክ ሃይል በሚፈልጉ ተቋማትና በሌሎች የመሠረተ ልማት አገልግሎት ሠጪዎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራርና መናበብ መኖር ይኖርበታል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በኢነርጂ የተትረፈረፈ ሀይል የማምረት አቅም ያላቸው አገሮች የኤሌክትሪክ የሃይል ሽያጭን ወደ ጎረቤት ሀገሮች በመላክ ዓይነተኛ የገቢ ምንጭ ማድረግ ግባቸው ነው፡፡ ከራስ ፍጆታ የሚተርፍን የኤሌክትሪክ ሀይል ለጎረቤት ሀገራት በመሸጥ ከሚገኘው ሽያጭ ሀገራዊ አቅምን መገንባት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ችግሮችን መፍታት፣

ከሀገሮችም ጋር በሰጥቶ መቀበል መርህ መልካም ጉርብትና ለመመስረት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ከሽያጩ በሚገኘው ገቢ ለቀጣይ ለሚገነቡ ፕሮጀክቶች ወጪም ጭምር የሚያግዝና ሀገሪቱን የምስራቅ አፍሪካ የታዳሽ ሀይል ማዕከል ለማድረግ የታያዘውን እቅድ ለማሳካት የኤሌክትሪክ የሀይል ሽያጭ ከፍተኛ ጉልበት ይኖረዋል፡፡

ሀገራችን በ2006 ዓ.ም ብቻ ለሱዳን 100 ሜጋዋት፣ ለጂቡቲ 60 ሜጋ ዋት እንዲሁም ለኬንያ 10 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ከ 70 ሚሊዮን  የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ችላለች፡፡ ምንም እንኳን በበጀት ዓመቱ የታቀደው የኤሌክትሪክ የኃይል ሽያጭ ገቢ 54 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ቢሆንም የእቅዱን 84 በመቶ በማከናወን ውጤታማ መሆን ተችሏል፡፡ የሀይል ሽያጩንም ለማሳደግ ከተለያዩ ሀገሮች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶች የተፈረሙ ሲሆን ይህም የሀገሪቱን ስትራጂክ አጋርነት የሚጨምርና በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የጂኦፖለቲካ ወሳኝ ሆኖ ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት በማገዝና የጎረቤት ሀገሮች ኢኮኖሚ ጭምር እንዲያድግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጎን ለጎን የታቀደው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ሀገሪቱ ካላት ዕምቅ የታዳሽ ሀይል አማራጭ ጋር ተዳምሮ ሀገሪቱ አሁንና ወደ ፊት የሚያስፈልጋትን የሀይል አቅርቦት ችግር እንዳይገጥመው ከወዲሁ የኢኮኖሚ አቅምን ማሳደግ ይገባል፡፡ ይህንኑ ከግምት በማስገባት ወደፊት የሚያስፈልገውን የኢነርጂ ፍላጎትና አቅርቦት ታሳቢ ያደረገ ስራም በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ያላትን ታዳሽ ሀይል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ በማዋል እንዲሁም የተረፈውን ደግሞ ወደ ውጭ በመላክ ከምታገኘው የውጭ ምንዛሬ ባሻገር 50 ሚልዮን ቶን ለአየር ንብረት ዋነኛ መንስዔ የሆኑ ሙቀት አማቂ ጋዞችን መቀነስ የሚያስችላት በመሆኑ የሀይል ዘርፉ ግንባታ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ብልፅግና ዋልታ በመሆኑ አጠናክሮ መሄዱ ለነገ የማይተው ስራ ይሆናል፡፡

በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን ካርበን በመቀነስ ኢትዮጵያ ለዓለማችን ደህንነት ስጋት በመሆን ላይ የሚገኘውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም የሀገራትን ትብብር በሚጠይቀው የሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ወሳኝ ወቅት ላይ ዋና ተዋናይ መሆን ከሚፈጥረው ሀገራዊ ገፅታ ባሻገር ከካርበን ንግዱ ኢትዮጵያ

የሚበረከትላት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች ለሀገራችን እድገት የሚያበረክተው ድርሻም እንዲሁ ከፍተኛ ነው፡፡

የማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታ፣ በተለያዩ የኪሎ ቮልት አቅም ያላቸው የማሰራጫ መስመሮችና ጣቢያዎች ግንባታ የሚከናወኑና እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ናቸው፡፡ እንዲሁም ያረጁ መስመሮችን የመቀየርና የማከፋፈያ ጣቢየዎችን አቅም የማሳደግና የማስፋፍያ ስራዎች የአገልግሎት ዘርፍ እያከናወናቸው ካሉት ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ከየትኛውም በኩል የሚጠየቀውን የሀይል ፍላጎት ከመመለስ ባሻገር ለውጭም በሽያጭ የሚቀርበውን ሀይል እንደሚያሳድጉት እሙን ነው፡፡ ሀገሪቱ ወደተለመችው የመካከለኛ ገቢ ሀገራት ለመሰለፍ ለምታደርገው ራዕይና ጉዞ መሳካት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ዘርፉ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ የህዳሴያችንና ዋነኛ የኢኮኖሚያችን ምሰሶ እንዲሆንና የዜጎችንም ህይወት ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት እንዲያግዝ መንግስት የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡